የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራአንደኛ ዓመት ቁጥር ፲፰
አዲስ አበባ ጥር ፳፭ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

11th Year No.18
ADDIS ABABA 2nd February, 2005


ማውጫ


አዋጅ ቁጥር ፬፻፴፫/፲፱፻፺፯ ዓ.ም.

የተሻሻለው የፌዴራል የሥነምግባርና የጸረ ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ የወጣ አዋጅ... ገጽ. ፪ሺ፱፻፺፮


CONTENTS


Proclamation No. 433/2005

Revised Federal Ethics and Anti-Corruption Commission Establishment proclamation ..Page 2996


## አዋጅ ቁጥር ፬፻፴፫/፲፱፻፺፯

## የተሻሻለው የፌዴራል የሥነምግባርና የጸረ ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ

የኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝቦች ሙስና እና ብልሹ አሠራር የአንድን አገር ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ እድገት የሚገታ ተግባር መሆኑን የተገነዘቡ በመሆናቸው፣

አገሪቱ የተያያዘችውን የእድገት ጎዳና እና የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ለማፋጠንና ቀጣይነት ያለው እንዲሆን ሙስናን እና ብልሹ አሠራርን በቁጥጥር ሥር ማዋል አስፈላጊ በመሆኑ፣ ለዚህም ሙስናንና ብልሹ አሰራርን ለመሸከም የማይፈልግ እና ይህንኑ በብቃት ለመዋጋት ዝግጁ የሆነ ሕብረተሰብ መፍጠር አስፈላጊ በመሆኑ፣

ሙስናንና ብልሹ አሠራርን ለመመርመር፣ ለመክሰስ ለመቆጣጠርና ለመከላከል መልካም ሥነ ምግባር በኅብረተሰቡ ውስጥ እንዲስፋፋ በማድረግ ሙስናንና ብልሹ አሠራርን በብቃት መዋጋት እንዲቻል፣ የኮሚሽኑን አሰራርና እንቅስቃሴ የግልጽነትና የተጠያቂነት መርሆዎችን በሚገልጽ መልኩ እንዲሁም ኮሚሽኑ ሀላፊነቱን በተሻለ ብቃት እንዲወጣ በሚያስችለው መልኩ የኮሚሽኑን ማቋቋሚያ አዋጅ ለማሻሻል በማስፈለጉ፣

የኮሚሽኑን ስልጣንና ተግባር ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ህግ ጋር በተጣጣመ ሁኔታ ማሻሻል በማስፈለጉ፣

## PROCLAMATION NO. 433/2005

## The REVISED PROCLAMATION FOR THE ESTABLISHMENT OF THE FEDERAL ETHICS AND ANTI-CORRUPTION COMMISSION

**WHEREAS,** the Government and the Peoples of Ethiopia recognize that corruption and impropriety are capable of hindering the Social, Economic and Political development of any country;

**WHEREAS,** corruption and impropriety are to be checked in order to promote and sustain the development and the democratic process in Ethiopia; and to that end it has become necessary to create a society which shall not condone but rather prepared to effectively combat corruption and impropriety;

**WHEREAS,** it has been deemed necessary to amend the commission's establishment proclamation to make its operation and activities be guided with the principle of transparency and accountability, and carry out its activity with better efficiency; in order to effectively fight corruption and impropriety through investigation, prosecution, and prevention as well as through the promotion of ethical values in the society;

**WHEREAS,** it has become necessary to redefine the powers and duties of the Commission in line with the criminal Code of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;

ኮሚሽኑ በከባድ የሙስና ወንጀሎች ላይ ትኩረት አድርጎ እንዲንቀሳቀስ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

ኮሚሽኑ ከሌሎች አግባብነት ካላቸው የምርመራና የአቃቤ ህግ ተቋማት ጋር ስለሚሰራበት ሁኔታ ዝርዝር ድንጋጌዎችን መደንገግ በማስፈለጉ፣

በሌሎችም ግልጽነት በሚያንሳቸው አንዳንድ የአዋጁ ድንጋጌዎች ላይ ማሻሻያዎችን ማድረግ በማስፈለጉ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭/፩/ መሰረት የሚከተለው ታውጇል::

## ክፍል አንድ
## ጠ ቅ ላ ላ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የተሻሻለው የፌዴራል የሥነምግባርና የጸረ ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፬፻፴፫/፲፱፻፺፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

### ፪. ት ር ጓ ሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

፩/ "ኮሚሽን" ማለት የፌዴራል የሥነምግባር እና የጸረሙስና ኮሚሽን ነው::

፪/ "ኮሚሽነር እና ምክትል ኮሚሽነር" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የኮሚሽኑ ኮሚሽነር ወይም ምክትል ኮሚሽነር ነው::

፫/ "የመንግስት መስሪያ ቤት" ማለት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በመንግስት በጀት የሚተዳደር እና የፌዴራል መንግስቱ ሥራዎች የሚከናወኑበት ማናቸውም መስሪያ ቤት ነው::

፬/ "የመንግስት የልማት ድርጅት" ማለት የመንግስት ባለቤትነት ድርሻ በሙሉ ወይም በከፊል ያለበት ማናቸውም የፌዴራል መንግስት የልማት ድርጅት ወይም የአክሲዮን ኩባንያ ነው::



**WHEREAS,** it has become necessary to make the attention of the Commission focused on grand corruption;

**WHEREAS,** it has become necessary to lay down detailed provisions enabling the Commission to work in collaboration with other relevant investigation and prosecution institutions;

**WHEREAS,** it has become necessary to make amendments to certain provisions of the Commission's establishment proclamation lacking clarity;

**NOW, THEREFORE,** therefore, in accordance with article 55(1) of the constitution of the federal democratic republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows;

## Part One
## General

### 1. Short Title

This proclamation may be cited as the "Revised Federal Ethics and Anti-Corruption Commission Establishment Proclamation No. 433/2005.

### 2. Definition

In this Proclamation, unless the context requires otherwise:

1/ **"Commission"** means the Federal Ethics and Anti- Corruption Commission.

2/ **"Commissioner and Deputy commissioner"** means the Commissioner and the Deputy commissioner of the Commission respectively;

3/ **"Public Office"** means any office of the Federal Government the budget of which is fully or partially allocated by the Government and in which any government activity is performed;

4/ **"Public Enterprise"** means any Federal Public Enterprise or Share Company the ownership of which is fully or partly owned by the Government.

፭/ "የመንግሥት ባለሥልጣን" ማለት የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና የፌዴሬሽን ምክር ቤት አባሎች፣ ከሚኒስትር ደረጃ በላይ የሆኑ የፌዴራል መንግሥት ባለሥልጣኖች፣ ሚኒስትሮች፣ ሚኒስቴር ዴኤታዎች፣ ምክትል ሚኒስትሮች፣ ኮሚሽነሮች፣ ምክትል ኮሚሽነሮች፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች፣ የብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ም/ቤት አባሎች፣ ከክልል ቢሮ ኃላፊዎች በላይ ያሉ ባለሥልጣኖች፣ የክልል መንግሥት ቢሮ ኃላፊዎች፣ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች፣ የአዲስ አበባ መስተደድርና የድሬዳዋ መስተዳድር የምክር ቤት አባሎች፣ ከመስተዳድሮቹ ቢሮ ኃላፊዎች በላይ ያሉ ባለሥልጣኖች፣ የመስተዳድሮቹ ቢሮ ኃላፊዎች እና በተመሳሳይ ደረጃ ላይ የሚገኙ የፌዴራል፣ የክልል እንዲሁም የአዲስ አበባና የድሬደዋ መስተዳድሮች ባለሥልጣኖችን ይጨምራል፣

፮/ "የመንግስት ሠራተኛ" ማለት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፭ ውስጥ ከተጠቀሱት ውጭ ያለ በፌዴራል ወይም በክልል ወይም በአዲስ አበባ መስተዳድር ወይም በድሬዳዋ መስተዳድር የመንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም የልማት ድርጅት ውስጥ ተሹሞ፣ ተመድቦ፣ ተቀጥሮ፣ በህዝብ ተመርጦ የሚሰራ ሰው ነው፣

፯/ "የሥነምግባር አውታሮች" ማለት በመንግሥት አስተዳደር ውስጥ ምግባረ ብልሹ ባህርያትን በከፍተኛ ደረጃ ለመቀነስ እና ሙያዊ ብቃትን እና መልካም ሥነምግባርን ለማበረታታት የሚያገለግሉ ዘዴዎች፣ አካላት፣ ሥርዓቶች ወይም አስፈላጊ ሁኔታዎች እና የመሳሰሉት ናቸው::

፰ "ከባድ የሥነምግባር መጣስ" ማለት አግባብ ባለው የሥነምግባር ደንብ መሰረት ከሥራ ሊያሰናብት የሚችል ጥፋት ነው::

፱/ "ከባድ የሙስና ወንጀል" ማለት፣

ሀ. ከፍተኛ ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ ባላቸው የመንግስት መስሪያ ቤቶችና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ላይ የሚፈጸሙ ከፍተኛ የገንዘብ መጠንን ያካተቱ የሙስና ወንጀሎች ወይም፣

ለ. የመንግስት ባለሥልጣንን የሚመለከቱ የሙስና ወንጀሎች ወይም፣

ሐ. በአገር ሉአላዊነት፣ ኢኮኖሚ፣ ጸጥታ እንዲሁም በሕብረተሰቡ ኑሮ ላይ ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርሱ ወይም ሊያደርሱ የሚችሉ የሙስና ወንጀሎች ናቸው::

5/ **"Public Official"** means members of the House of People's Representatives and of the House of the Federation, officials of the Federal Government above ministerial rank, ministers, state ministers, vice ministers, commissioners, vice commissioners, judges of the Federal Supreme Court, members of Regional State Councils, officials of the Regional State above the Regional State bureau heads, Regional State Bureau heads, judges of the Regional State Supreme Court, Council members of the Addis Ababa City Administration and the Dire Dawa Administrative Council, officials of the Administration above Bureau heads, Bureau heads and such other officials of the Federal, Regional, Addis Ababa City Administration and Dire Dawa Administrative Council of equivalent rank.

6/ **"Public Employee"** means all persons, other than those referred to under sub-article 5 hereof, who are appointed, assigned, employed or elected and working in a public office or a public enterprise of the Federal Government, Regional State, Addis Ababa city Administration or Dire Dawa Administrative council.

7/ **"Ethics Infrastructures"** means mechanisms, bodies, or procedures or the necessary conditions and similar matters that will serve to reduce substantially unethical conducts and to encourage efficiency and integrity in the public service;

8/ **"Serious Ethical Violations"** means any ethical violation entailing dismissal as per appropriate code of conduet regulation.

9/ **"Serious Corruption Offence"** means

a) Corruption offences involving huge amount of money committed in highly strategic Public Office and Public Enterprise; or

b) Corruption offences involving a public official; or

c) Corruption offences which cause or capable of causing a grave danger to the national sovereignty, economy, security or social life.

፲/ “የባንክ ሂሳብ” ማለት በባንክ የተቀመጠ ገንዘብ፣ ወርቅና የመሳሰሉት ውድ እቃዎች እንዲሁም አንድ ደንበኛ ከባንኩ ጋር የሚያደርጋቸውን ማናቸውንም ግንኙነቶች/ትራንዛክሽኖች/ የሚያጠቃልል ነው::

፲፩/ “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው::

## ክፍል ሁለት
## ስለኮሚሽኑ መቋቋም እና ሥልጣንና ተግባር

### ፫. የኮሚሽኑ መቋቋም

፩/ የፌዴራል የሥነምግባር እና የጸረሙስና ኮሚሽን/ ከዚህ በኋላ ኮሚሽኑ እየተባለ የሚጠራ/ ራሱን የቻለ የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ መሠረት ተቋቁሟል::

፪/ የኮሚሽኑ ተጠሪነት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሆናል::

### ፬. ስለኮሚሽኑ የአሠራር ነፃነት

በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፫ ንዑስ አንቀጽ ፪ የተደነገገው ቢኖርም ኮሚሽኑ በሚመረምራቸው ወይም ክስ በሚመሰርትባቸው ወይም ክስ በመሰረተባቸው ጉዳዮች ላይ ከማንኛውም ሰው ወይም አካል ጣልቃ ገብነትና አመራር ነፃ ነው::

### ፭. ዋና መስሪያ ቤት

የኮሚሽኑ ዋና መስሪያ ቤት አዲስ አበባ ይሆናል:: ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በየክልሉ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶችን ሊያቋቁም ይችላል::

### ፮. የኮሚሽኑ ዓላማዎች

ኮሚሽኑ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል::

፩/ አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የሥነ ምግባር እና የጸረ ሙስና ትምህርቶችን በማስፋፋት የነቃ እና ሙስናን ሊሸከም የማይችል ሕብረተሰብ እንዲፈጠር ጥረት ማድረግ፣

፪/ አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የሙስና ወንጀልን እና ብልሹ አሠራርን መከላከል፣

፫/ የሙስና ወንጀልን እና ብልሹ አሠራርን ማጋለጥ፣ መመርመር እና መክሰስ፣

10/ **"Bank Account"** means money, gold and similar precious materials and includes any transactions made through the bank.

11/ **"Person"** means natural or juridical person.

## Part Two
## Establishment and Powers and Duties of the Commission

### 3. Establishment of the Commission

1/ The Federal Ethics and Anti-Corruption Commission (hereinafter referred to as "the Commission") is hereby established as an independent Federal Government body.

2/ The Commission shall be accountable to the Prime Minister.

### 4. Independence of the Commission

Notwithstanding the provisions of Sub-Article 2 of Article 3 of this Proclamation, the Commission shall be free from any interference or direction by any person with regard to cases under investigation or prosecution or to be investigated or prosecuted.

### 5. Head Office

The Commission shall have its head office in Addis Ababa and may establish branch offices in the Regions as may be necessary.

### 6. Objectives of the Commission

The Commission shall have the following objectives:

1/ In cooperation with relevant bodies, to strive to create an aware society where corruption will not be condoned or tolerated by promoting ethics and anti-corruption education;

2/ In cooperation with relevant bodies, to prevent corruption offences and other improprieties;

3/ To expose, investigate and prosecute corruption offences and impropriety.

**፯. የኮሚሽኑ ስልጣንና ተግባር**

ኮሚሽኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል::

፩/ አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር ስለሙስና ጎጂነት የህዝቡ ንቃተ ህሊና እንዲጎለብት በማስተማር እና መልካም ሥነምግባር በሕዝብ አገልግሎት እና በኅብረተሰቡ ውስጥ እንዲስፋፋ በማድረግ ሙስናንና ብልሹ አሰራርን መዋጋት፣

፪/ አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር በመንግስት መ/ቤቶች እና በመንግስት የልማት ድርጅቶች ውስጥ ለሙስናና ለብልሹ አሰራር የተጋለጡና ሊጋለጡ የሚችሉ የአሰራር ሥርዓቶችን በማጥናት ወይም እንዲጠኑ በማድረግ እንዲሻሻሉ ማማከርና ማሳሰብ፣ የአሰራር ስርዓቶቹ የተሻሻሉ መሆናቸውን መከታተል እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ተገቢ የሆነው እርምጃ እንዲወሰድ ወይም ውሣኔ እንዲሰጥ አግባብ ላለው አካል በማሳወቅ ወይም በማሳሰብ ሙስናን የመከላከል፣ በሌሎች ሰዎች ሲጠየቅ ተመሳሳይ ምክርና ድጋፍ የመስጠት፣

፫/ በመንግስት መ/ቤቶች እና በመንግስት የልማት ድርጅቶች ውስጥ ከባድ የሥነምግባር መጣስ ስለመፈጸሙ ጥቆማ ሲደርሰው ወይም በቂ ጥርጣሬ ሲኖረው የማጣራት ወይም እንዲጣራ የማድረግ እና ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ የመከታተል፣

፬/ በመንግስት መ/ቤቶች ወይም በመንግስት የልማት ድርጅቶች ወይም ፌዴራል መንግስቱ ለክልሎች ከሚ ሰጠው ድጎማ ጋር በተያያዘ በክልል መ/ቤቶች በወን ጀል ህግ እና በሌሎች ሕጎች ውስጥ የተመለከቱት የሙስና ወንጀሎች በመንግስት ሰራተኞች ወይም ባለስልጣኖች ወይም በሌሎች ሰዎች ስለመፈጸማቸው ጥቆማ ሲደርሰው ወይም በቂ ጥርጣሬ ሲኖረው የመመርመርና የመክሰስ ወይም እንዲመረመር ወይም እንዲከሰስ የማድረግ፣

፭/ ከሙስና ወንጀል ጋር በተያያዘ በቂ ጥርጣሬ ሲኖረው በማናቸውም ባንክ የሚገኝ የተጠርጣሪዎች የባንክ ሂሳብ በኮሚሽነሩ ትእዛዝ እንዲመረመር የማድረግ፣ መረጃ የማግኘት እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በፍርድ ቤት ትእዛዝ እንዲከበር የማድረግ፣

፮/ ከሙስና ወንጀል ጋር በተያያዘ በምርመራ ላይ ያሉ ሰዎች ሀብት በፍርድ ቤት ትእዛዝ እንዳይንቀሳቀስ ማድረግ፣ በሙስና ወንጀል የተገኘ ለመሆኑ የተረጋገጠን ወይም በሙስና ወንጀሉ ከተገኘው ጥቅም ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ማናቸውንም ንብረት ወይም ሀብት በፍርድ ቤት ትእዛዝ እንዲወረስና በሐራጅ ተሸጦ ወይም ሳይሸጥ ለመንግሥት ገቢ እንዲሆን የማድረግ፣

፯/ አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በህግ በሚደነገገው መሠረት የመንግሥት ባለስልጣኖችን እና በህግ ሀብታቸውንና የገንዘብ ጥቅማቸውን እንዲያስመዘግቡ ግዴታ ያለባቸውን የመንግሥት ሰራተኞች ሀብትና የገንዘብ ጥቅሞች መዝግቦ የመያዝ ወይም ተመዝግበው እንዲያዙ የማድረግ፣

**7. Powers and Duties of the Commission**

The Commission shall have the powers and duties:

1/ In cooperation with relevant bodies, to combat corruption and other impropriety by creating, awareness through educating the public about the effects of corruption and the promotion of ethics in public service and in the society;

2/ In cooperation with relevant bodies, to prevent corruption by studying or causing to be studied the practices and procedures in Public Offices and Public Enterprises to secure the revision of methods of work which may be conducive to corrupt practices as well as follow up their implementation; and inform or remind the relevant body, when deemed essential, to take the proper measures or give decision, and advise or assist on same, upon request, any other persons;

3/ To investigate or cause the investigation of any complaints of alleged or suspected serious breaches of the codes of ethics in public offices or public enterprises; and follow up the taking of proper measures;

4/ To investigate and prosecute or cause the investigation and the prosecution of any alleged or suspected corruption offences specified in the criminal code or in other laws where they are committed by public officials or public employees or other persons in Public Offices or Public Enterprises, or in the Regional offices relating to subsidies granted by the Federal Government to the Regions;

5/ Where there is reasonable suspicion in connection with corruption offences, to investigate and obtain information about, with the order of the commissioner, any bank account of suspected persons; and cause the attachment, with court order of same where necessary;

6/ To freeze, by court order, the assets of any person who may be under investigation for corruption; and cause, through court order, the forfeiture of any assets and wealth obtained by corruption or its equivalent to the state or dispose same by or without public auction;

7/ In cooperation with relevant bodies, to register or cause the registration of the assets and financial interests of public officials and other public employees compellable to do so as specified by law;

፰/ አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር ለሙስና ወንጀል ጠቋሚዎችና ምስክሮች የአካልና የሥራ ዋስትና ጥበቃ የሚሰጥበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣ በህግ በሚወሰን መሰረት ጥበቃ የመስጠት፣

፱/ ሙስናን በመታግል እና በመከላከል ረገድ ጥሩ ውጤት ያስገኙ ሰዎችን እና መ/ቤቶችን አወዳድሮ ለሽልማት የሚበቁበትን ሥርአትና መለኪያ የመዘርጋት፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ የማድረግ፣

፲/ የሕግ አውጪና የዳኝነት አካላትን ሳይጨምር ለመንግስት መስሪያ ቤቶችና ለመንግስት የልማት ድርጅቶች የሚያገለግሉ የሥነ ምግባር ደንቦች መዘጋጀታቸውን ማረጋገጥ ወይም ማዘጋጀት እና አፈጻጸማቸውን የመከታተል፣ ከሕግ አውጭ እና ከዳኝነት አካላት ጥያቄ ሲቀርብለት በሥነምግባር ደንብ አዘገጃጀት ረገድ ምክር የመስጠት፣

፲፩/ አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የሥነምግባር አውታሮችን የማስተባበር፣

፲፪/ አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የሥነምግባርን እና ሙስናን በተመለከተ ጥናትና ምርምር የማድረግ እና ተመሳሳይ ሥራዎችን የመደገፍ፣ የኮሚሽኑን አላማዎች ለማራመድ የሚረዱ ሪፖርቶችን እና ቴክኒካዊ ጥናቶችን አሳትሞ የማሰራጨት፣

፲፫/ አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የጸረሙስና ህጎች መከበራቸውን የመከታተል እና የማረጋገጥ ስለአፈጻጸማቸው የምክር አገልግሎት የመስጠት፣

፲፬/ በመንግስት መስሪያ ቤቶችና የልማት ድርጅቶች ውስጥ የስነምግባር መከታተያ ክፍሎች እንዲቋቋም ድጋፍ የማድረግ፣

፲፭/ ለክልሎች አስፈላጊውን የምክርና የድጋፍ አገልግሎት የመስጠት፣

፲፮/ ተመሳሳይ አላማ ካላቸው አገራዊ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ አካላት ጋር ግንኙነትና ትብብር የመፍጠር፣

፲፯/ የንብረት ባለቤት የመሆን፣ ውል የመዋዋል፣ በራሱ ስም የመክሰስና የመከሰስ፣

፲፰/ በሕግ የሚሰጡትን እና ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን የማከናወን::

8/ In cooperation with relevant bodies, to facilitate the condition, for the protection of physical and job security of witnesses and whistleblowers, provide protection of the same in accordance with the law.

9/ To establish and implement, upon approval, procedures and standards for the selection of awards, upon competition, of persons or offices who are successful in fighting and preventing corruption;

10/ Apart from legislative and judicial bodies, to ensure the preparation or to prepare and monitor the implementation of codes of ethics for Public Offices and Public Enterprises; to provide upon request, advice to legislative and judicial bodies in establishing their own codes of ethics;

11/ In cooperation with relevant bodies, to coordinate other components of the ethical infrastructures;

12/ In cooperation with relevant bodies, to undertake research on ethics and corruption; give support to other similar activities and to publish reports and technical studies to further the purpose of the commission;

13/ In cooperation with relevant bodies, to follow up and ensure the enforcement of anti-corruption laws and give advice on the implementation of same;

14/ To provide the necessary support to the Public Offices and Public Enterprises in the establishment of ethics liaison units;

15/ To provide the necessary advice and support to the regions;

16/ To liaise and cooperate with national, regional and international bodies with similar objectives;

17/ To own property, enter into contract, to sue and be sued in its own name;

18/ To perform such other duties as may be defined by law and undertake other activities necessary for the attainment of its objectives:

## ፰. በሌሎች አካላት ስለሚደረግ የሙስና ወንጀል ምርመራ

፩/ ኮሚሽኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፯ ንዑስ አንቀጽ ፬ ከተሰጠው ሥልጣን ውስጥ ከባድ ያልሆነ የሙስና ወንጀልን የመመርመር ጠቅላላ ውክልና በሙሉ ወይም በከፊል እንደሁኔታው ለፌዴራል ወይም ለክልል የወንጀል መርማሪ አካላት ሊሰጥ ይችላል::

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት ውክልና ያልተሰጠው ማንኛው ወንጀልን ለመመርመር ስልጣን ያለው የፌዴራል ወይም የክልል መንግስታዊ አካል በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፯ ንዑስ አንቀጽ ፬ በኮሚሽኑ የስልጣን ክልል ስር የሚወድቅ የሙስና ወንጀል ለመፈጸሙ ጥቆማ ሲደርሰው ወይም በቂ ጥርጣሬ ሲኖረው ምርመራ መጀመር ይኖርበታል:: ሆኖም ስለተጀመረው ምርመራ ለኮሚሽኑ ሳይዘገይ ያሳውቃል::

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ በተመለከተው መሰረት ኮሚሽኑ ሪፖርት ሲደርሰው:-

ሀ. ጉዳዩን እራሱ ወስዶ ይመረምራል ወይም

ለ. ከባድ የሙስና ወንጀልን ጨምሮ ምርመራው ሪፖርት ባደረገው የምርመራ አካል ወይም በሌላ አካል እንዲከናወን ሊያደርግ ይችላል:: ዝርዝሩ ኮሚሽኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል::

፬/ ኮሚሽኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሰረት ባሚቀርብለት ሪፖርት መሰረት መልስ ሳይሰጥ ከቀረ ምርመራውን የጀመረው አካል የተጀመረውን ምርመራ በማጠናቀቅ የምርመራ ፋይሉን ክስ ለመመስረት ስልጣን ላለው አካል ያስተላልፋል::

፭/ ኮሚሽኑ በቀጥታ በሚደረሰው ጥቆማ ወይም በሌላ መልኩ በሚያገኘው መረጃ መሰረት የጀመራቸውን የሙስና ወንጀል ምርመራዎች በሌሎች የምርመራ አካላት እንዲመረመር ሊያደርግ ይችላል:: ማንኛውም በዚህ ንዑስ አንቀጽ መሰረት የምርመራ ፋይል የተላለፈለት አካል ምርመራውን ማከናወን ይኖርበታል::

፮/ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ ፪ እስከ ፭ በተመለከተው መሠረት በሌሎች የምርመራ አካላት ስለሚከናወኑ የሙስና ወንጀል ምርመራዎች ሪፖርት ስለሚደረግበት ሁኔታ ኮሚሽኑ ዝርዝር መመሪያ ያወጣል፣ ለሚመለከታቸው የምርመራ አካላት ያሳውቃል::

## ፱. በሌሎች የፍትህ አካላት የሙስና ወንጀል ክስ ስለመመስረት

፩/ ኮሚሽኑ ከአቃቤ ህግነት ስልጣኑ ውስጥ አግባብነት ላለው የፌዴራል ወይም የክልል አቃቤ ህግ ወይም የስነምግባርና የጸረ ሙስና ተቋም በሙሉ ወይም በከፊል ውክልና ሊሰጥ ይችላል::

## 8. Investigation of Corruption Offences by Other Organs

1/ The Commission may delegate, in whole or in part, to Federal or Regional crime investigation bodies, as the case may be, a general investigation power of corruption cases, other than grand corruption, from that it is vested under sub art 4 of Article 7 of this Proclamation.

2/ Any Federal or Regional crime investigation body that is not delegated under sub article 1 of this Article shall begin investigation of any alleged or suspected corruption offences falling under the competence of the commission. It shall, however, inform the commission of same forthwith.

3/ The Commission may, upon receipt of the report as specified in sub article 2 of this Article

a) investigate the matter by itself, or

b) cause its investigation, including grand corruption; be undertaken by the reporting investigation organ or other organ, as the case may be. Details shall be provided for in directives to be issued by the commission.

4/ Where the Commission fails to react on the report it received under sub article 2 of this Article, the organ commencing investigation shall finish and send same to the competent organ.

5/ The Commission may cause the investigation of corruption offences it has started investigating be undertaken by other investigating organs. Any such organ shall undertake the investigation.

6/ The Commission shall issue directives concerning the manners of reporting of corruption offences investigation carried out by other investigating bodies as provided in sub articles 2 to 5 of this article and notify same to all concerned investigating bodies.

## 9. Prosecution of Corruption Offences by Other Justice Organs

1/ The Commission may delegate, in whole or in part, to Federal or Regional prosecution offices or regional anti- corruption institutions, as the case may be, its power of corruption prosecution.

፪/ ከፌዴራል መንግስት ለክልል መንግስታት ከተሰጠ የበጀት ድጎማ ጋር በተያያዘ የክልል የስነምግባርና ጸረሙስና ተቋም ወይም ስልጣን ያለው አቃቤ ህግ ክስ መመስረት ይችላል:: ሆኖም ኮሚሽኑ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው በማንኛውም ጊዜ የክልሉን የሥነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ተቋም ወይም አቃቤ ህግ በመተካት በክርክሩ ውስጥ ሊገባ ይችላል::

**፲. የኮሚሽኑ አቋም**

ኮሚሽኑ፣

፩/ በጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅራቢነት በተወካዮች ምክር ቤት የሚሾም አንድ ኮሚሽነር፣

፪/ በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሾም አንድ ምክትል ኮሚሽነር እና

፫/ ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች፣
ይኖሩታል::

**፲፩. የኮሚሽኑ አቃቤ ህግ አደረጃጀት**

የኮሚሽኑ አቃቤ ህግ ሙያዊ ነጻነቱን ለመጠበቅ በሚያስችል መልኩ ነጻ ሆኖ ይደራጃል::

**፲፪. የኮሚሽነሩ ሥልጣንና ተግባር**

፩/ ኮሚሽነሩ የኮሚሽኑ ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን የኮሚሽኑን ሥራዎች ያደራጃል፣ ይመራል፣ ያስተዳድራል፣

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚሽነሩ፣

ሀ. በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፯ የተዘረዘሩትን የኮሚሽኑን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፣

ለ. በዚህ አዋጅ በተመለከተው መሰረት እና የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕግ አጠቃላይ መርሆዎችን መሠረት በማድረግ በሚወጣው የአስተዳደር ደንብ መሠረት የኮሚሽኑን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል::

ሐ. ኮሚሽነሩ በዚህ ህግ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕግ አጠቃላይ መርሆዎችን መሠረት በማድረግ የኮሚሽኑን የአስተዳደር ደንብ አዘጋጅቶ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ያቀርባል:: ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል::

2/ Regional anti-corruption or prosecution offices may institute corruption offence proceedings in the regional offices relating to subsidies granted by the federal government to the regions. The Commission, when it deems necessary, may at any time substitute the Regional anti-corruption office or prosecutor and enter into the proceeding.

**10. Organization of the Commission**

The commission shall have;

1/ A Commissioner to be appointed by the house of peoples' representatives upon nomination by the Prime Minister;

2/ A Deputy Commissioner to be appointed by the Prime Minister; and

3/ The necessary staff.

**11. Organization of the Commission's Prosecution**

The Commission's prosecution shall be organized and structured in such a way that ensures its professional independence.

**12. Powers and Duties of the Commissioner**

1/ The Commissioner shall be the chief executive of the Commission and, as such, shall organize, direct and administer the activities of the Commission;

2/ Without limiting the generality stated in Sub-Article 1 of this article, the Commissioner shall have powers and duties:

a) to exercise the powers and duties of the Commission specified under article 7of this Proclamation;

b) to employ, administer and dismiss officers of the Commission in accordance with the provisions provided for in this Proclamation and the administrative regulation of the Commission to be issued in line with the basic principles of Civil Service Laws;

c) to prepare, following the provisions laid down in this proclamation and the general principles of the federal Civil Service Law, and submit the administrative regulation to the Prime Minister and implement upon approval.

መ. የኮሚሽኑን ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራም እና በጀት አዘጋጅቶ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል::

ሠ. ለኮሚሽኑ በተፈቀደለት በጀት እና ባዘጋጀው የሥራ ፕሮግራም መሰረት የፋይናንስ ሕግን ተከትሎ ገንዘብ ወጪ ያደርጋል::

ረ. በሙስና ወንጀል የተጠረጠሩ ሰዎችን የኮሚሽኑ ሠራተኞች በህግ መሠረት ለመመርመር፣ ለመክሰስ ወይም ለማሰር እንዲችሉ ሥልጣን ይሰጣል::

ሰ. ምርመራው በመከናወን ላይ ላለ ጉዳይ አግባብነት ያለው በሆነ ጊዜ የማንኛውም ሰው ወይም ድርጅት የባንክ ሂሣብ እንዲፈተሽ እና አስፈላጊው መረጃ እንዲሰበሰብ ትእዛዝ ለመስጠት ይችላል::

ሸ. ኮሚሽኑ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ኮሚሽኑን ይወክላል::

ቀ. የኮሚሽኑን ጠቅላላ የሥራ አፈጻጸምና የሂሳብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ያቀርባል::

፫/ ኮሚሽነሩ ለኮሚሽኑ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለኮሚሽኑ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል::

## ፲፫. የምክትል ኮሚሽነሩ ሥልጣንና ተግባር

፩/ ምክትል ኮሚሽነሩ፣

ሀ/ የኮሚሽኑን ተግባሮች በማቀድ፣ በማደራጀት፣ በመምራትና በማስተባበር ኮሚሽነሩን ይረዳል::

ለ/ በኮሚሽኑ መዋቅር መሰረት የሥራ ክፍፍል በማድረግ ከኮሚሽኑ ዘርፎች ከፊሉን ይከታተላል::

ሐ/ ኮሚሽነሩ በማይኖርበት ጊዜ እሱን ተክቶ ይሰራል::

መ/ ከኮሚሽነሩ ተለይተው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል::

፪/ ምክትል ኮሚሽነሩ ተጠሪነቱ ለኮሚሽነሩ ይሆናል::

d) to prepare the annual work program and budget of the Commission and submit to the Prime Minister. Implement same upon approval;

e) to effect expenditure in accordance with approved budget and work program of the Commission and in accordance with the financial laws;

f) to authorize, in accordance with the law, any officer of the commission to carry out investigation or prosecution or to arrest persons who are suspected of corruption;

g) to issue warrants to search and obtain information therefrom, of any bank account of any person or organization if there is reasonable suspicion that such is relevant to a case under investigation;

h) to represent the Commission in its dealings with third parties.

i) to submit performance and financial reports to the Prime minister.

3/ The Commissioner may delegate part of his powers and duties to other officials and employees of the Commission to the extent necessary for the effectiveness and efficiency of the Commission.

## 13. Powers and Duties of the Deputy Commissioner

1/ The Deputy Commissioner, shall:

a) assist the Commissioner in planning, organizing, directing and coordinating the functions of the commission

b) follow up part of the Commission's departments by sharing functions in accordance with the structure of the Commission;

c) act on behalf of the Commissioner in the absence of the latter;

d) perform such other duties as may be specifically entrusted to him by the Commissioner.

2/ The Deputy Commissioner shall be accountable to the Commissioner.

## ፲፬. የኮሚሽነሩና የምክትል ኮሚሽነሩ የሥራ ዘመንና ከሥራ መነሳት

፩/ የኮሚሽነሩና የምክትል ኮሚሽነሩ የሹመት ዘመን ለስድስት ዓመት ይሆናል፣ ሆኖም አስፈላጊ ሲሆን እንደገና ሊሾም ይችላል::

፪/ ኮሚሽነሩ ወይም ምክትል ኮሚሽነሩ ከዚህ በታች በተመለከቱት ሁኔታዎች ካልሆኖ በስተቀር የተሾመበት የሥራ ዘመን ከማለቁ በፊት ከፈቃዱ ውጭ ከሥራው አይነሳም፣

ሀ. አግባብነት ባለው የስነምግባር ደንብ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ተላልፎ ሲገኝ፣

ለ. ጉልህ የሆነ የሥራ ችሎታና ቅልጥፍና የሌለው ሲሆን፣

ሐ. በህመም ምክንያት ተግባሩን በተገቢው ሁኔታ ማከናወን የማይችል ሆኖ ሲገኝ፣

## ፲፭. ስለኮሚሽኑ ሠራተኞች ቅጥር ሁኔታ

የኮሚሽኑ ሠራተኞች የቅጥር አስተዳደርና ስንብት ሁኔታ በዚህ አዋጅ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች እና የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ህግ አጠቃላይ መርሆዎችን መሠረት በማድረግ በሚወጣው የአስተዳደሩ ደንብ መሠረት ይሆናል::

## ፲፮. ቃለመሀላ ስለመፈጸም

በኮሚሽኑ የተቀጠረ ማንኛውም ሰራተኛ ለፌደራሉ ህገመንግስት ታማኝ በመሆን የተጣለበትን ህዝባዊ አደራና ሙያዊ ሀላፊነት ለመወጣት ቃለመሀላ ይፈጽማል:: የቃለመሀላው ዝርዝር ይዘት በአስተዳደር ደንቡ ይወሰናል::

## ፲፯. የኮሚሽኑ ሰራተኛ መብት

፩/ ማንኛውም የኮሚሽኑ ሠራተኛ በመንግስት በሚፀድቅ የደመወዝ ስኬል መሰረት ደመወዝ ያገኛል::

፪/ የማንኛውም ሠራተኛ ደመወዝ፣

ሀ/ በሠራተኛው ስምምነት፣

ለ/ በፍርድ ቤት ትእዛዝ

ሐ/ በህግ በተደነገገው

መሰረት ካልሆነ በስተቀር ሊያዝ ወይም ሊቆረጥ አይችልም::



## 14. Term of Office and Removal from Office of the Commissioner and the Deputy Commissioner

1/ The term of appointment of the Commissioner or the Deputy Commissioner shall be for six years; he may, however, be reappointed where necessary.

2/ Once appointed, the Commissioner or the Deputy Commissioner may not be removed, except on his own will, from his office unless;

a) he has violated the provisions of the relevant code of conduct;

b) he has shown manifest incompetence and inefficiency

c) he can no longer carry out his responsibilities on account of mental or physical illness.

## 15. Employment of Officers of the Commission

The terms and conditions of employment, administration and dismissal of the officers of the Commission shall be in accordance with the regulations to be issued following the provisions laid down in this Proclamation and the general principles of the Federal Civil Service Law.

## 16. Taking of an Oath

Any person shall take oath upon employment in the Commission declaring that he carry out his functions with diligence and utmost commitment to the constitution so that he fulfill the demands of public trust and professional responsibility bestowed on him. Contents of the oath shall be determined by the administrative regulation.

## 17. Rights of officers

1/ Any officer of the Commission is entitled to a salary in accordance with the salary scale approved by the Government.

2/ The salary of any officer may not be attached or deducted except in accordance with,

a) the consent of the officer, or

b) court order, or

c) provisions of the law.

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪/ለ/ ወይም /ሐ/ መሰረት ከሰራተኛ ደመወዝ በየወሩ የሚቆረጠው ከደመወዙ አንድ ሶስተኛ አይበልጥም::

፬/ ማንኛውም የኮሚሽኑ ቋሚ ሠራተኛ በጡረታ ሕግ መሰረት የጡረታ መብት ይኖረዋል::

፭/ የኮሚሽኑ ሠራተኛ፣

ሀ/ ሥራውን በተገቢው መንገድ በመወጣት ላይ እያለ ለሚደርስበት ተጠያቂነት በመስሪያ ቤቱ ወጪ ድጋፍና የጥብቅና አገልግሎት ያገኛል:: ዝርዝር አፈጻጸሙ በደንብ ይወሰናል::

ለ/ በማንኛውም አጋጣሚ የበላይ ሀላፊዎችን በአግባቡ የመጠየቅ፣ ስህተት ሲያይ የመጠቆም፣ በውይይት ችግሮችን የመፍታት እንዲሁም የሰልጣን ተዋረድን ጠብቆ አቤቱታ ማቅረብ ይችላል::

ሐ/ በአስተዳደር ደንቡ በሚወሰን መሠረት ይግባኝ የማቅረብ መብት ይኖረዋል::

መ/ ከሥራው ጋር በተያያዘ ሁኔታ በሚደርስበት ጉዳት ዘላቂ ሙሉ ወይም ከፊል የመስራት ችሎታውን ያጣ የኮሚሽኑ ሠራተኛ አግባብ ባለው የጡረታ ህግ የተሰጠው መብት ይከበርለታል:: ሠራተኛው ጊዜያዊ የመንግስት ሠራተኛ ከሆነና ዘላቂ ሙሉ የመስራት ችሎታውን ያጣ ከሆነ የሚከፈለው የጉዳት ካሣ መጠን የአንድ ዓመት ደመወዙ በአምስት ተባዝቶ የሚገኘው የክፍያ መጠን ይሆናል::

ሠ/ "ጊዜያዊ ሠራተኛ ከሆነና የደረሰው ጉዳት ዘላቂ ከፊል የመስራት ችሎታ ማጣት ከሆነ የሚከፈለው የጉዳት ካሣ መጠን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፭ /መ/ በተመለከተው ክፍያ ላይ የተመሠረተ ሆኖ ከመስራት ችሎታ ማጣቱ ደረጃ ጋር ተመጣጣኝ ይሆናል"

ረ/ "የደረሰበት ጉዳት ከባድ የአካል ወይም የመልክ መበላሸትን ያደረሰ ከሆነ የመስራት ችሎታ ማጣትን ባያስከትልም በዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች አፈፃፀም እንደዘላቂ ከፊል የመስራት ችሎታ ማጣት ይቆጠራል::"

ሰ/ በትርፍ ጊዜው ከሥራው ጋር የጥቅም ግጭት በማይፈጥር ሥራ ላይ መስሪያ ቤቱን በማሳወቅ ለመስራት ይችላል:: ዝርዝሩ ኮሚሽኑ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይወሰናል::

3/ The amount deductible in accordance with sub article 2 (b) or (c) of this Article may not exceed one third of the salary of the officer.

4/ Any permanent officer of the Commission is entitled to a pension in accordance with the Pension law.

5/ Any officer of the Commission shall:

a) be provided with attorney service at the expense of the Commission for any liability incurred while executing his duties properly. Particulars shall be determined by the administrative regulation.

b) have the right to appropriately question superiors under any circumstances, inform mistakes, resolve problems through discussion as well as lodge complaints following the chains of command;

c) has the right to appeal as to be determined in the administrative regulation.

d) be entitled to benefits provided in the relevant pension law for permanent, total, or partial disability sustained in relation to his duties. Where the officer who has sustained permanent total disability is a temporary officer, he shall be entitled to compensation amounting to five times of his annual salary.

e) receive an amount of compensation to be calculated on the basis of the sum referred to in sub-article 5(d) of this article and proportional to the degree of disability, where he is a temporary officer and the disability he sustained is permanent partial.

f) where the injury he sustained causes serious deformity although not resulting in disability, it shall be considered permanent partial disability for the purpose of this Article.

g) May, after informing the Commission, engage in any other activity, which may not have a conflict of interest with his duty, during his leisure time. Details shall be the subject of regulations to be issued by the Commission.

## ፲፰. ከግብር ነጻ ስለመሆን

በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከፈል የጡረታ አበል ወይም የጉዳት ካሣ ክፍያ ከግብር ነፃ ይሆናል። እንዲሁም በእዳ ሊከበር ወይም በማቻቻያነት ሊቀነስ ወይም ባለመብቱ ሊያስተላልፈው አይችልም።

## ፲፱. ከሥራ ስለማገድ

፩/ የኮሚሽኑ ሠራተኛ ከሥራ ታግዶ መቆየት ለሥራው አፈፃፀም ጠቃሚ ሆኖ ከተገኘ ሠራተኛውን ከአንድ ወር ለማይበልጥ ጊዜ ከሥራና ደወመዝ አግዶ ለማቆየት ይቻላል።

፪/ የኮሚሽኑ ሠራተኛ በወንጀል ወይም በዲሲፕሊን ጥፋት በህግ የተከሰሰ እንደሆነና ሲመሰከርበት ጥፋቱ ከስራው የሚያስወጣው መሆኑ ሲገመት ከስራ ታግዶ መቆየት አለበት፡

## ፳. ስለይርጋ ጊዜ

፩/ ቀላል የዲሲፕሊን ቅጣት የሚያስከትል ጥፋት የፈፀመ የመንግሥት ሠራተኛ የምርመራውን ጊዜ ሳይጨምር የፈፀመው ጥፋት ከታወቀበት ቀን ጀምሮ እስከ ስድስት ወር እርምጃ ካልተወሰደበት በዲሲፕሊን ተጠያቂ አይሆንም፣

፪/ ከባድ የዲሲፕሊን ቅጣት የሚያስከትል ጥፋት የፈፀመ የኮሚሽኑ ሠራተኛ የፈጸመው ጥፋት ከታወቀበት ቀን ጀምሮ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በጥፋቱ ካልተከሰሰ በዲሲፕሊን ተጠያቂ አይሆንም።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ ወይም /፪/ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ መወሰድ የሚገባውን የዲሲፕሊን እርምጃ ሳይወስድ የቀረው ኃላፊ ተጠያቂ ይሆናል።

## ፳፩. በ ጀ ት

፩/ የኮሚሽኑ በጀት በመንግስት ይመደባል።

## ፳፪. የሂሣብ መዛግብት

፩/ ኮሚሽኑ የተሟሉ እና ትክክለኛ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል።

፪/ የኮሚሽኑ የሂሣብ መዛግብት እና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በፌዴራሉ ዋና ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራል።



## 18. Exemption from tax

Any pension allowance or compensation to be made pursuant to this proclamation shall be exempt from taxation and may not be attached, deducted by way of setoff or assigned by the beneficiary.

## 19. Suspension from duty

1/ An officer of the Commission may be suspended from duty by withholding his salary for a period not exceeding one months if that course of action is necessary for the smooth execution of the work.

2/ An officer shall be suspended if he is formally charged with a criminal or disciplinary offence for which his dismissal is to be expected if it is proved against him.

## 20. Period of Limitation

1/ Disciplinary measure shall not be taken against an officer who has committed an offense entailing simple disciplinary penalty unless such measure is taken with six months, excluding the time required for investigation from the time the breach of discipline is known.

2/ No disciplinary charge shall be brought against an officer who has committed an offense entailing rigorous disciplinary penalty unless such disciplinary charge is brought within a year from the time the commission of the offense is known.

3/ The official who has failed to take the measures specified under Sub-Article 1 or 2 of this Article shall be held responsible.

## 21. Budget

The budget of the commission shall be allocated by the Government

## 22. Books of Accounts

1/ The Commission shall keep complete and accurate books of accounts.

2/ The Commission's books of accounts and financial documents shall be audited annually by the Federal Auditor-General.

## ክፍል ሦስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፳፫. ስለኮሚሽኑ የፖሊስነትና የዐቃቤ ህግነት ሥልጣን**

ስለመመርመርና ስለመክሰስ በወንጀለኛ መቅጫ ህግ ሥነ-ሥርዓትና በሌሎች ህጎች ለፖሊስና ለዐቃቤ ህግ የተሰጠ ሥልጣን በዚህ አዋጅ ውስጥ የተመለከቱ ጉዳዮችን በሚመለከት ለኮሚሽኑ ተሰጥቶአል::

**፳፬. የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች መቋቋም**

፩/ በየደረጃው በሚገኙ የመንግስት መሥሪያ ቤቶች እና ልማት ድርጅቶች ውስጥ የሥነ ምግባር ሁኔታን የሚያስተባብሩ እና ለየመስሪያ ቤቶቹ የበላይ ኃላፊዎች የሚያማክሩ የሥነ ምግባር መከታተያ ክፍሎች ይቋቋማሉ::

፪/ የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ተጠሪነቱ ለመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ወይም ለልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ይሆናል::

፫/ የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ኃላፊ ወይም ሠራተኛን የመስሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ በቅጥር፣ በእድገት ወይም በዝውውር ይመድባል፣ ለሥራ መደቡ የሚያስፈልገውን የትምህርትና የሥራ ልምድ እንዲሁም የሥነምግባር ሁኔታ በሚመለከት ከኮሚሽኑ ጋር በመመካከር ይወስናል::

፬/ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሉ ከኮሚሽኑ ጋር የሚኖረውን የሥራ ግንኙነት በሚመለከት በዝርዝር በደንብ ይወሰናል::

**፳፭. በኮሚሽንና በክልል ተቋሞች መካከል ስለሚኖረው የሥራ ግንኙነት**

፩/ ሙስናን መሸከም የማይችል ህብረተሰብ በመፍጠር እንዲሁም ሙስናን በመከላከል፣ በመመርመርና በመክሰስ ኮሚሽኑ ከክልል የሥነምግባር የጸረ-ሙስና ተቋሞች ጋር በቅንጅትና በተደጋጋፊነት ይሰራል::

፪/ የክልል መስሪያ ቤቶች በኮሚሽኑ በሚሰጣቸው ውክልና መሠረት የሙስና ወንጀል ጉዳዮችን ሲመረምሩና ሲከሱ ተጠሪነታቸው ለኮሚሽኑ ይሆናል::

፫/ ኮሚሽኑና የክልል የሥነምግባርና የጸረ-ሙስና ተቋሞች ለፀረ-ሙስና እንቅስቃሴው ስኬት በጋራ ለሚያከናውኗቸው ተግባራትና የሚያከናውኗቸውን ተግባራት አፈጻጸም ለመገምገም የሚወያዩበት የጋራ ጉባኤ ሊያቋቁሙ ይችላሉ:: የኮሚሽኑ ኮሚሽነር የጋራ ጉባኤውን ይመራል:: የጋራ ጉባኤው፣



## Part Three
## Miscellaneous Provisions

**23. The Police and Prosecution Power of the Commission**

The investigation and prosecution powers of the police and public prosecutor specified under the Criminal Procedure Code and other laws are hereby given to the Commission with regard to matters specified in this Proclamation.

**24. Establishment of Ethics Liaison Units**

1/ There shall be established Ethics Liaison Units at every level of Public Offices and Public Enterprises the duty of which shall be to coordinate ethical issues and advise the heads of he concerned bodies.

2/ The liaison unit shall be accountable to the head of the concerned public office or public enterprise.

3/ The liaison unit's head or employee may be assigned by the head of the concerned public office or public enterprise through employment, promotion or transfer. The qualification, work experience and ethical standards required for the post may be determined in consultation with the Commission.

4/ The liaison unit's work relation with the Commission shall be specified by regulations.

**25. Relations of the Commission with the Regional Institutions**

1/ The Commission shall work in cooperation and mutually supportive way with the Regional ethics and anti-corruption institutions in areas of creating an aware society which cannot tolerate corruption, as well as corruption prevention, investigation and prosecution.

2/ The Regional Institutions shall be accountable to the Commission when they investigate and prosecute in accordance with the delegation given to them.

3/ The Commission and the Regional ethics and anti-corruption institutions may form a joint forum where they may deliberate on the success of their anti-corruption activities and evaluate their performance. The commissioner shall preside over such forum. The joint forum shall:

ሀ. የጋራ የአሠራር ውስጠ ደንብ ያወጣል፡፡

ለ. ሙስናን በመከላከልና በመመርመር እንዲሁም መልካም ሥነምግባርን በማስፈን የሥራ እንቅስቃሴዎችን በመገምገም የልምድ ልውውጥ ያደርጋል

ሐ. ሥልጠናን በሚመለከት የጋራ አቅጣጫዎችን ይቀይሳሉ፡፡

መ. በኮሚሽኑ ወይም በክልል የሥነምግባርና የጸረሙስና ተቋሞች በሚቀርቡ ጥናቶች ላይ ይወያያል፣ በጥናቶቹ መሠረት ሊወሰድ የሚገባቸው እርምጃዎች እንዲወሰኑ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፣ እንደሁኔታው ይወስናል፣ በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፡፡

፬/ ኮሚሽኑና የክልል የሥነምግባርና የጸረ ሙስና ተቋሞች የጋራ ጉባኤ ያስተላለፋቸውን ውሣኔዎች መተግበራቸውን በየበኩላቸው ይከታተላሉ፡፡

፭/ የክልል የሥነምግባርና የጸረ ሙስና ተቋሞች በክልላቸው ስላለው የሙስና ወንጀል ሁኔታ በሚመለከት ሪፖርትና ስታቲስቲክስ በየጊዜው ለኮሚሽኑ ያስተላልፋሉ፡፡

**፳፮. የሙስና ወንጀልን የማስታወቅና የመተባበር ግዴታ**

፩/ የመንግሥት መስሪያ ቤቶችና የመንግሥት የልማት ድርጅቶች በራሳቸው የሚወስዱት የአስተዳደር ወይም የዲሲፕሊን እርምጃ እንደተጠበቀ ሆኖ ከባድ የሥነምግብር መጣስና የሙስና ወንጀል የተፈጸመ ለመሆኑ ጥርጣሬ ሲኖራቸው ወዲያውኑ ለኮሚሽኑ ወይም ስልጣን ላለው የምርመራ አካል ሪፖርት የማድረግ ግዴታ አለባቸው፡፡

፪/ ማንኛውም የመንግሥት ባለስልጣን ወይም የመንግሥት ሠራተኛ በመስሪያ ቤቱ የሙስና ወንጀል ተፈጽሞአል ወይም ሊፈጸም በዝግጅት ላይ ነው ብሎ በሚጠረጥርበት ጊዜ ለኮሚሽኑ ወይም ሥልጣን ላለው የምርመራ አካል የማስታወቅ ግዴታ አለበት፡፡

፫ ማንኛውም ሰው ከኮሚሽኑ ሥልጣንና ተግባር ጋር በተያያዘ ለሚጠየቀው ትብብርና ድጋፍ የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡ በተለይም ኮሚሽኑ የሙያ ድጋፍን በሚመለከት ለሚያቀርባቸው ጥያቄዎች አግባብነት ያላቸው የመንግሥት መስሪያ ቤቶችና የልማት ድርጅቶች አስፈላጊውን ድጋፍ መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡

a) draw up its own internal regulations;

b) exchange experiences in matters of corruption prevention, investigation and prosecution as well as in the promotion of ethics;

c) devise joint directions with respect to training;

d) deliberate on studies presented by the Commission or Regional ethics and anti-Corruption institutions; forward recommendations and measures to be taken on the basis of the study to the proper government body, and ensure their implementation.

4/ The Commission and the Regional ethics and anti-Corruption institutions on their part shall follow up the implementation of decisions adopted by the forum.

5/ The Regional Ethics and anti-corruption institutions shall submit statistical data and periodic report regarding the state of corruption offences in their respective region to the Commission.

**26. Duty to Inform and Cooperate**

1/ Public offices and Public Enterprises shall, without prejudice to administrative or disciplinary measures they take, report to the Commission serious ethical violations and corruption offences forthwith.

2/ Any public official or public employee in a Public Office or Public Enterprise shall report to the Commission where he has reasonable suspicion that corruption offences are or are about to be committed.

3/ Any person is duty bound to cooperate whenever cooperation and assistance is required by the Commission in connection with its powers and duties. In particular Public Offices and Public Enterprises having the necessary expertise shall provide the Commission with the necessary professional support when required.

፬/ በዚህ አዋጅ መሰረት የሙስና ወንጀልን ለመመርመር ሥልጣን ያለው ማንኛውም መርማሪ በማንኛውም ጊዜ በፌዴራል ሆነ በክልል የመንግስት መስሪያ ቤት ወይም የልማት ድርጅት በመገኘት ለምርመራ ሥራው አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች እንዲሰጠው ወይም እንዲመለከት መጠየቅ ይችላል:: በማንኛውም በፌዴራልም ሆነ በክልል የመንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም የልማት ድርጅት ያለ ኃላፊ ወይም ሠራተኛ የሙስና ወንጀልን ለመመርመር ሥልጣን ባለው መርማሪ ሲጠየቅ አስፈላጊውን መረጃ የማሳየት ወይም የማቅረብ ግዴታ አለበት::

## ፳፯. ቅ ጣ ት

በሌላ ህግ የበለጠ የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር፣

፩/ ማንኛውም ሰው ለኮሚሽኑ፣ ለፍትሕ አካላት ወይም ለመንግሥት መሥሪያ ቤት ኃላፊ ወይም የልማት ድርጅት ኃላፊ ከሙስና ወንጀል ጋር በተያያዘ መረጃ ወይም ማስረጃ በሰጠ ሰው ላይ ተጽዕኖ ለማድረግ ወይም ጉዳት ለማድረስ የሞከረ ወይም ያደረሰ ወይም ይህንኑ ሰው ለመቅጣት የሞከረ ወይም የቀጣ እንደሆነ ከሦስት ዓመት በማያንስ፣ ከአሥራ አምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት እና ከስድስት ሺህ ብር በማያንስ፣ ከሃያ አምስት ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል::

፪/ ማንኛውም የኮሚሽኑ ኃላፊ ወይም ሠራተኛ በሕግ የተሰጠውን ሥልጣንና ኃላፊነት ያለአግባብ የተገለገለበት እንደሆነ፣ በዚያም የተነሳ ያገኘው ጥቅም መወረሱ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከአምስት ዓመት በማያንስ፣ ከአሥራ አምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት እና ከሦስት ሺህ ብር በማያንስ፣ ከአሥር ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል::

፫/ ማንኛውም ሰው ሆን ብሎ ኮሚሽኑን ለማሳሳት ወይም ሌላውን ሰው ለመጉዳት ሐሰተኛ ሪፖርት ጥቆማ ወይም መረጃ ለኮሚሽኑ ያቀረበ እንደሆነ ከአንድ ዓመት በማያንስ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራትና ከሦስት ሺህ ብር በማያንስ ከአስር ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል::

፬/ ማንኛውም ሰው የኮሚሽኑ ሠራተኛ መስሎ በመቅረብ የማታለል ሥራ የፈጸመ እንደሆነ ከሦስት ዓመት በማያንስ ከአስር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት እና ከአምስት ሺህ ብር በማያንስ ከአስራ አምስት ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል::



4/ Any investigator who has the power to investigate corruption offences may require the production or examination of relevant documents or information from any Federal or Regional Public Office and Public Enterprise. Any public official or public employee in a public office or public enterprise of a Federal or Regional Government shall show or produce relevant documents or information when required by any investigator who has the power to investigate corruption offences.

## 27. Penalty

Unless it is punishable with more severe penalty under other laws;

1/ Whosoever attempts to influence, harm or punish or who influences, harms or punishes any person who gives evidence or provides information relating to corruption offences to the Commission, organs of judicial administration, head of a Public office, or a Public enterprise shall be punishable with rigorous imprisonment not less than three years and not exceeding fifteen years; and with fine not less than Birr six thousand and not exceeding Birr twenty five thousand.

2/ Any official or staff of the Commission who abuses the powers and responsibilities legally entrusted to him shall, in addition to the forfeiture of any advantage gained therefrom, be punishable with rigorous imprisonment not less than five years and not exceeding fifteen years, and with fine not less than Birr three thousand and not exceeding Birr ten thousand.

3/ Whosoever, with the intent to mislead the Commission or to injure others, submits a false report, allegation or evidence to the Commission shall be punishable with rigorous imprisonment not less than one year and not exceeding five years; and with fine not less than Birr three thousand and not exceeding Birr ten thousand.

4/ Whosoever commits a deceitful act by pretending to be the staff of the Commission shall be punishable with rigorous imprisonment not less than three years and not exceeding ten years; and with fine not less than Birr five thousand and not exceeding Birr fifteen thousand.

፭/ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፳፮ ንዑስ አንቀጽ ፫ ወይም ፬ በተደነገገው መሠረት ከሚሽኑን ለመተባበር እምቢተኛ የሆነ እንደሆነ ከስድስት ወር በማያንስ ከአራት ዓመት በማይበልጥ እስራት እና ከአንድ ሺህ ብር በማያንስ ከአምስት ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል::

፮/ ማንኛውም ሰው የኮሚሽኑን ሥራ ያደናቀፈ ወይም ለማደናቀፍ የሞከረ እንደሆነ ከሁለት ዓመት በማያንስ ከአስር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት እና ከአምስት ሺህ ብር በማያንስ ከሃያ ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል:: ወንጀሉ የተፈጸመው ኃይል በመጠቀም የሆነ እንደሆነ ቅጣቱ በዚሁ ንዑስ አንቀጽ የተደነገገው ከፍተኛ ቅጣት ይሆናል::

፯/ የሙስና ወንጀል ምርመራ ሊጀመር ስለመሆኑ ወይም በምርመራ ላይ ስለመሆኑ ወይም ጉዳዩ በምርመራ ላይ መሆኑን እያወቀ ስለተፈጸመው ድርጊት ምርመራውን ከያዘው ክፍል ፈቃድ ውጭ መግለጽ፣ መጻፍ፣ ማሰራጨት ከስድስት ወር በማያንስ ከአራት ዓመት በማይበልጥ እስራት እና ከአንድ ሺህ ብር በማያንስ ከአምስት ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ያስቀጣል::

፰/ ማንኛውም የመንግሥት ባለሥልጣን ወይም የመንግሥት ሠራተኛ በሚሰራበት መስሪያ ቤት የሙስና ወንጀል ስለመፈጸሙ እያወቀ ሳያሳውቅ መቅረት እስከ አምስት ዓመት ቀላል እስራት እና እስከ አስር ሺህ ብር መቀጮ ያስቀጣል::

፱/ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ ፩፣ ፫፣ ፬፣ ፭ እና ፮ የተመለከቱት ወንጀሎች በወንጀል ህግ መሠረት ተጠያቂ በሚሆን የህግ ሰውነት ባለው ድርጅት በተፈጸሙ ጊዜ የገንዘብ ቅጣቱ አምስት እጥፍ ይሆናል::

## ፳፰. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

በአዋጅ ቁ. ፪፻፴፭/፲፫ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት ተፈጽመው ምርመራቸው በሌሎች አካላት በጅምር ወይም በሂደት ላይ ያለም ሆነ የተጠናቀቀ ወይም በፍርድ ቤት በመታየት ላይ ያሉ የሙስና እና ከሙስና ጋር የተያያዙ የወንጀል ጉዳዮች በነበሩበት ሁኔታ ቀጥለው ውሳኔ ያገኛሉ::

5/ Whosoever refuses to cooperate with the Commission as provided for in sub article 3 or 4 of article 26 of this article shall be punishable with simple imprisonment not less than six months and not exceeding four years; and with fine not less than Birr one thousand and not exceeding Birr five thousand.

6/ Whosoever obstructs or attempts to obstruct the activities of the Commission shall be punishable with rigorous imprisonment not less than two years and not exceeding ten years; and with fine not less than Birr five thousand and not exceeding Birr twenty thousand. Where the offence is accompanied by violence, the maximum penalty prescribed in this sub-article shall be imposed.

7) Whosoever publicize, disseminate, distribute without the authorization of the investigator that an investigation of corruption offence is to commence or underway, or about the act of corruption knowing that the case is under investigation, shall be punishable with imprisonment not less than six months and not exceeding four years; and with fine not less than one thousand Birr and not exceeding five thousand Birr.

8) Any public official or public employee who, knowing the commission of a corruption offence in his respective office, fails to inform shall be punishable with simple imprisonment not exceeding five years and with fine not exceeding ten thousand Birr.

9/ Where the offences specified in Sub-Articles 1, 3, 4, 5 and 6, of this article are committed by juridical persons, responsible under the penal code, the punishment with a fine shall be five fold.

## 28. Transitory provision

Any corruption cases or other cases related with corruption which have been committed prior to the coming into force of proclamation no 235/2001 and the investigation of which have been just started, or undergoing, or finalized, or which have been in the process of trial, shall continue to be handled and decided in the same manner

**፳፱. የተሻሩና ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች**

፩/ የፌዴራል የሥነመግባርና የጸረሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁ. ፪፻፴፭/፲፱፻፺፫ በዚህ አዋጅ ተሽሯል::

፪/ ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረኑ ማናቸውም ሌሎች ህጎች በዚህ አዋጅ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም::

**፴. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም ደንብ ሊያወጣ ይችላል::

፪/ ኮሚሽኑ ይህንን አዋጅና በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጣውን ደንብ ለማስፈጸም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል::

**፴፩. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ ከጥር ፳፭ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል::

አዲስ አበባ ጥር ፳፭ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም.

ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

**29. Repealed and inapplicable laws**

1/ Proclamation no. 235/2001 is hereby repealed.

2/ All laws which are inconsistent with this Proclamation shall not apply on matters covered under this Proclamation.

**30. Powers to Issue Regulations and Directives**

1/ The Council of Ministers may issue Regulations for the implementation of this Proclamation.

2/ The Commission may issue Directives for the implementation of this Proclamation and the Regulations issued under this Proclamation.

**31. Effective Date**

This Proclamation shall come into force as of the 2nd day of February, 2005.

**Done at Addis Ababa, this 2nd day of February, 2005.**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL**
**DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**